



## 1. ኩራት ሞኝ ያደርጋል

ስለ ራስ ትልቅነት ማሰብና መታበይ ሞኝነት ነው። በቁንጅናዋ የምትታበይ ኮረዳ፥ በእውቀቱ የሚኩራራ ጎበዝ፣ ቁንጅናውንና እውቀቱን የሰጣቸውን አምላክ የሚገባውን ክብርና ምስጋና መከልከላቸው ነው። በትዕቢት መንፈስ የተያዘ ሰው ሌሎች ስለሚያደርጉት በጎ አገልግሎት ማመስገን ያስቸግረዋል። ሌሎቹም ሲያመሰግኗቸው መስማት አይወድም። የሙሴ መንፈሳዊነትና ዝናው በገነነበት ጊዜ፥ በሁኔታው ደስ ያልተሰኘችው የገዛ እህቱ ማርያም "እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ነው እንዴ የሚናገረው…በእኛም እኮ ይናገራል" አለች። አባባሏ ከጥሩ ስሜት የመጣ እንዳልነበረ በደረሰባት ቅጣት መረዳት እንችላለን። ይሄ ችግር በሙሴ ዘመን ብቻ የነበረ ሳይሆን ዛሬም ቢሆን በግልጽ ይታያል። ሰው በራሱ ፍጹም ያልነበረውን ነገር እንዲኖር አድርጎ መፍጠር ካልቻለ፥ ሠርቶ የሚያሳየው ከሌለው የተቀበለው ነውና፥ ለፈጣሪው ተገቢውን ክብር ከልክሎ በራስ መኩራራት ሞኝነት ነው።

## 2. ኩራት ተሸናፊ ያደርጋል

በስፖርት ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ሆነው ቀርበው የማሸነፍ ዕድል እያላቸው የሚሸነፉ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። የሚሸንፉት ችሎታና ዘዴ አንሷቸው ሳይሆን ብዙዎቹ በራሳቸው በመተማመን ሲዝናኑ ነው። ብዙዎች ደግሞ ራሳቸውን እንደአዋቂ በመቁጠር ከትምህርት ዓለም እንደራቁ ይቀራሉ። በመንፈሳዊ ሕይወትም ደግሞ አሸናፊ ሕይወት መኖር እየቻሉ በራሳቸው በመታመን ብቻ ተሰናክለው የሚወድቁ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። ጠቢቡ ሰለሞን "ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩሩ መንፈስም ወድቀትን ይቀድማል" ሲል ትክክለኛ አባባል ነው። ምንም እንኳን ታሪኩ ተረት ይሁን እንጂ፥ ጠቃሚ ትምህርት ያዘለ በመሆኑ ከዚህ በፊት በተረት መጽሐፍት ውስጥ ያነበባችሁትን የአንዲት እንቁራሪት ታሪክ ልናስታውሳችሁ እንወዳለን። አንዲት እንቁራሪት ብርድና ውርጭ ከነበረበት ሥፍራ ተነስታ ሙቀት ወደሆነበት ሥፍራ ለመሄድ ተነሳች። ሥፍራው ሩቅ በመሆኑ በእግሯ መዝለቅ እንደማትችል የተረዱ ሁለት ወዳጆቿ የነበሩ ወፎች እንዴት ሊረዷት እንደሚችሉ መንገድ ካላት ችግሯን ለማቃለል ፈቃደኝነታቸውን ገለጹላት። ብልሃተኛዋ እንቁራሪት ረጅም ገመድ አምጥታ የገመዱን ጫፍና ጫፍ ይዘው ሲበሩ እርሷ ደግሞ መካከል ሆና በአፏ ገመዱን አጥብቃ በመያዝ አብራቸው መብረር ጀመረች። በሁኔታው በጣም የተደነቀ ገበሬ 'ይሄ መቼም ግሩም ጥበብ ነው፥ ለመሆኑ ማን የፈጠረው ሃሳብ ነው?" ብሎ ጠየቀ። ያቺ እንቁራሪት ምንም እንኳን በአፏ ገመዱን ብትይዝም፥ አዋቂነቷን ለመናገር ያጋጠማት ዕድል እንዳያመልጣት በመቻኮል "እኔ የፈጠርኩት ዘዴ ነው" ብላ መልስ ስትሰጥ ከመሬት ተፈጥፍጣ ሞተች። ኩራት ውድቀትን እንደሚያስከትል በተረት መጽሐፍ ብቻ የተጠቀሰ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስም ያረጋግጥልናል።

## 3. ኩራት ከእግዚአብሔር ይለያል

ኩራት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አንድነት ያበላሻል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለጸሎት ወደ መቅደስ ስለገቡ ሁለት ሰዎች እናነባለን። አንደኛው ፈሪሳዊ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ቀራጭ ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች በባህሪያቸው ፍጹም የተለየዩ ነበሩ። ፈሪሳዊው ብዙ የሚኮራባቸው ባህሪዎች ነበሩት። በህብረተሰቡ የተከበረ፣ ንጹህ ሕይወት የነበረው፣ የሰው ዕዳ ያልነበረበት፣ አሥራቱን በታማኝነት የሚሰጥ፣ ፍጹም

የሃማኖት ሰው ነበር። ቀራጩ ግን በኃጢአቱ የተነሳ የነበረበት ኅብረተሰብ የናቀውና የጠላው ሰው ነበር። ሁለቱም ሰዎች ጸሎታቸውን በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ። ፈሪሳዊው ሲጸልይ “እግዚአብሔር ሆይ፣ አመሰግንሃለሁ እንደሌሎች ሰዎች ሌባ፣ ነጣቂ ስላላደርግኸኝ…በሳምንት ሁለት ጊዜ እጸልያለሁ፤ አሥራቴን አከፍላለሁ…” አለ። ይህ ፈሪሳዊ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ የራሱን ትልቅነት ዘረዘረ። እንዲያውም “እኔን የመሰለ ጥሩ አገልጋይ በማግኘትህ እግዚአብሔር ሆይ ዕድለኛ ነህ” ሳይለው አልቀረም። ቀራጩ ግን በራሱ የሚኩራበት ምንም ነገር አልነበረውም። በኃጢአቱ ምክንያት እግዚአብሔርን ያሳዘነ መሆኑን በመረዳት አንገቱን ቀና አድርጎ እንኳን ለመጸለይ አለደፈረም። ደረቱንም እየደቃ “እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለኝ” አለ። የእነዚህ የሁለት ሰዎች ጸሎት ውጤት ምን ሆነ? ፈሪሳዊው የጸሎቱ ውጤት መና ሆነ። ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር ስላልወደደው ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ሊሰጠው ያቀደውን በረከት ለመቀበል ስለተኩራራ ብቻ ነው። “በራሴ ጻድቅ ነኝ” ስላለ የሚያስፈገውን የእግዚእብሔርን ወዳጅነት ሳያገኝ ቀረ። ቀራጩ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ የሆነውን አንድነት መሥርቶ ጻድቅ ሆኖ ተመለሰ። ኩራት የእግዚአብሔርን መንግሥት መዝጋት ብቻ ሳይሆን፥ ብዙዎቹን ከክርስቶስ መንግሥት ያስወጣል። በክርስቶስ አንድነት ደስ የሚለው ትሁት ሰው ብቻ ነው። በራሱ ብቃት እንዳለው የሚገምት ሁሉ ከክርስቶስ ዕርዳታን ለመቀበል ወደ እርሱ አይሄድም። ሰው ዕርዳት ያስፈልገኛል ብሎ ራሱ ፈቅዶ ካልመጣ እግዚአብሔር በግድ ገፍቶ የሰው መብት ነክቶ አይገባም።

## 4. ኩራት ሰውን ጨካኝ ያደርጋል

ኩራት በሰው ሕይወት ፈራጅ ያደርጋል። የሌላውን ሰው ጥሩ ሥራ በመመልከት ፈንታ የተበላሸበትን አቅጣጫ መመልከት ይወዳል። ቀደም ሲል የጠቀስነው ፈሪሳዊ ሲጸልይ፥ ሌሎችን ሌቦችና ቀማኞች አድርጎ ሲያቀርብ፥ ራሱን ግን ጻድቅ አድርጎ አቀረበ። ስለራሱ ጥሩ ጥሩውን ነገር ሲመለከት፥ የሌሎችን ኃጢአታቸውን ሲዘረዝር በመካከሉ እግዚአብሔርን ማየት ተሳነው። ኩራተኛ ሰው በፍርድ አሰጣጡ ብቻ ሳይሆን በባህሪውም ጨካኝ ነው። “ሁልጊዜ እኔ ልክ ነኝ…ሌሎች ግን ስህተተኞች ናቸው” ስለሚል ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር መኖር በጣም ያስቸግራል። ከሌላው ሰው ጋር ተጋጭቶ ሌላው ሰው ቢጎዳው፥ ይቅርታ ለማድረግ ያስቸግረዋል። ወይንም እርሱ የሌሎችን ስሜት ቢጎዳ “አዝናለሁ በድያለሁ” ብሎ ይቅርታ መጠየቅ በጣም ያስቸግረዋል። ኩራተኛ ሰው ሌላውን በድሎ ይቅርታ በመጠየቅ ነጻ ከመሆን ይልቅ በህሊና ክስ መሰቃየትና ያለ እንቅልፍ መኖርን ይመርጣል።

## 5. ኩራት ደስታን ያጠፋል

“በመንፈስ ድሆች የሆነ ብጹአን/ደስተኞች ናቸው” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ትሁቶች ደስተኞች ከሆኑ ኩሩዎች ደስታ የራቃቸው ናቸው ማለት ነው። ያልሆኑትን እንደሆኑ መስለው በማቅረባቸው የህሊና ወቀሳ ስለሚያጠቃቸው ደስታ የራቃቸው ይሆናል። እንግዲህ የክርስትና ሕይወት ነቀዝ ከሆነው የኩራት መንፈስ ነጻ ለመሆን እግዚአብሔር ይርዳን።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**